ክቡራን ወላጆች (ቤተ-ሰብ)

ትምህርቲ ኣስፈላጊ ነው። መከንይቱ ደግሞ ልጆቻችሁ በጀርመን ኣገር ውስጥ፣ መልካም ህይወት ስለሚያስፈልጋቸው ነው። ከዚህ በመነሳት፣ በዚህ ጽሁፍ ኣድርገን የትምህርት ኣስፈላጊነት የሚግልጽ መረጃ በተለይ በራይንላንድ ፋልስ ክፍለ-ሃገር እናስተዋውቃችሁ ኣለን።

በራይንላንድ ፋልስ ክፍለ-ሃገር፣ ትምህርት ገና በመዋእለ-ህጻናት (ኪንደር-ጋርተን)ነው የሚጀምረው። በሌላ እነጋገር ደግሞ፣ መዋእለ-ህጻናት ማለት ትርጉሙ፣ ህጻናት ቀኑን ሙሉ ይሚውሉበት መጠለያ ሆኖ፣ ለህጻናት ብቻ የሚፈቀድ ቦታ ማለት ነው። ስለዚ ልጆቻቹሁ እዛው በመዋእለ-ህጻናት ውስጥ በሚቆዩበት ግዜ፣ ከለሎች ልጆች ጋር ኣብረው የሚጫወቱበት ዕድልና፣ ጓደኞች የሚያገኙለት እጋጣሚ ይፈጥራል ማለት ነው። በተለይ ደግሞ፣ ልጆቻችሁ እዛው በመዋእለ-ህጻናት (ኪንደርጋርተን) ውስጥ በሚውሉበት ወቅት፣ ኣብረው ከሌሎች ህጻናት ስጫወቱ፣ በተለይ የጀርመን ቋንቋ በቀላሉ ለመማር ስለሚችሉ ነው።

ስለዚህ፣ ልጆቻችሁ በተቻለ መጠን፣ ብግዜውና ገና ደግምፕ ብህጻንነታቸው ሳሉ፣ በመዋእለ-ህጻናት ሲመዘገቡ ወይም ስገቡ በጣም ትልቅ ዕድል ነው። በራይንላንድ ፋልስ ክፍለ-ሃገር፣ ማንኛውም ህጻን ከኣንድ ዓመት ዕድሜው ጀምሮ፣ በመዋእለ-ህጻናት ለመዋል መብቱ የተጠበቀ ነው። ስለዚህ እናንተ ወላጆች ፈቃደኞች ከሆናችሁ፣ ልጃችሁ በመዋእለ ህጻናት፣ ቦታ ለማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው። የህጻኑ ዕድሜ ኣስከ ሁለት ዓመት ከሆነ ደግሞ፣ በመዋእለ ህጻናት ገንዘብ ሳይከፍል በነጻ ኣንዲውል ይፈቀድለታል።

በመዋእለ-ህጻናት የሚያገለግሉ የህጻናት ኣሳዳጊዎች ወይ ባለሞያዎች ከነሱ ተነጋገሩ። በተለይ ደግሞ ልጃችሁ ለመጀመርያ ግዜ በመዋእለ ህጻናት በሚገባበት ወቅት፣ ለኣንድ ሳምንት ይምያህል ህጻኑን በመሸኘት ወይም ከህጻኑ ጋር ወደ በመዋእለ ህጻናት እየሄዳችሁ፣ ህጻኑ መዋኣለ-ህጻናቱ  መውደዱና ወይ መጥላቱ ለማወቅ ትችላላችሁ። ይኸ ደግሞ ለኛ በጣም ኣስፈላጊ ጉዳይ ነው። እኛ በጀርመን ኣገር፣ ኣናንተ ወላጆች፣ በመዋእለ ህጻንት እየሄዳችሁ፣ ከነዛው የህጻናት ኣሳዳጊዎች ወይም ባለሞያዎች ጋር ስትነጋገሩና ስትግባቡ ወይም እምነት ስታሳድሩና፣ ጥያቄዎች ደግሞ ስትጠይቁ በጣም እንፈልጋለ። ስለዚ ሁሉ ግዜ ስለ ልጆቻችሁ ጉዳይ በመዋእለ ህጻናት እየሄዳችሁ ጠይቁ።

ህጻናት ወደ መዋእለ-ህጻናት ስሄዱ፣ ወጣቶች ደግሞ ወደ ትምህርትቤት ስሄዱ፣ ለኣንድ ኣገር ትልቅ እርምጃ ነው። በትምህርት ጎበዝ መሆንና ጥሩ የትምህርት ውጤት ማውጣትና፣ በጀርመን ውስጥ ጥሩ ኑሮ መኖር የሚያስችልና፣ ጥሩ ስራ እንድታገኝ ዕድል የሚሰጥ ወይም የሚከፍት ኣንድ ትልቅ ጉዳይ ነው። መከንያቱም ትምህርት ለማንም ሰው ኣስፈላጊ ስለሆ፣ ወደ ትምህርትቤት ምሄድ ግዳጅ ነው። በሊላ ኣነጋገር፣ የፈደራላዊ ጀርመን ህግ በሚፈቅደው መሰረት፣ ማንኛውም ልጅ (ህጻን) ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እንዳለበት፣ የትምህርት ህግ ኣንቀጽ §§56 ያስገድዳል። ልጃችሁ በትምህርት በጣም ድል

እንድያደግር ዘንድ፣ የጀርመንኛ ቋንቋ በደምብና ቶሎ ብሎ መማር አለበት። በዚህ መሰረት እንግዲህ በራይንላንድ ፋልስ ክፍለ-ሃገር የሚገኙት ኣብያተ ትምህርቶች እንድ ተማሪ በቶሎ ጀርመንኛ ቋንቋ ለመማር አስቸኳይ የትምህርት ዕድል ከፍቶዋል ወይም ኣዘጋጅቶዋል።

በዚህ የትምህርት ወይም የኮርስ ዕቅድ፣ ትምህርት ቤቶች ለ20 ሰዓቶች የኒይህል የጀርመንኛ ቋንቋ ለማቅረብ ተዘጋጅቷል። ስለዚህ ከጀርመንኛ ቋንቋ ትምህርት ጎንለጎን ደግሞ፣ ልጆቻችሁ ከመጀመርያ ጀምሮው ከጀርመኖች ወንዶችና ሴቶች ኣብረው ይማራሉ። ህጻኑ የጀርመንኛ ቋንቋ እየተማረ ሳለ፣ ጎንለጎን ደግሞ ከጀርመናውያን ጋር ጓደኝነት ይፈጥራል ወይም ጓደኞት የማግኘት አድል ያገኛል። የሚማረውን ትምህርት ደግሞ፣ ለምስሌ፣-የስእልና የሙዚቃ ወይም የስፖርት ትምህርት ያጠናቅቃል። ልጃችሁ የእንግልዝኛ ቋንቋ የሚያውቅ ከሆነ ደግሞ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋው ይማራል ወይም ያሻሽላል።

እንድ ጥሩ ትምህርት ቤት የሚባል፣ በታማኝነት የሚሰራና፣ ከመምህራን እና ከተማሪዊች ጋር ደግሞ የሚግባባና የሚተባበር መሆን ይገቧል። እዛው ትምህርት ቤት ውስጥ ደግሞ። ስለ ስርዓተ ትምህርት መረጃ ወይም መግለጫ ልታገኙ ትችላችሁ።

ስለዚህ በትምህርት ቤቶች በኩል፣ ኣስተማሪዎችና፣ የትምህርት ቤቶች ስራ-ኣስከያጆችን በመጠየቅ መረጃ ልታገኙ ትችላላችሁ።

በጀርመን ኣገር እንግዲህ፣ ለናንተ ለወላጆችና፣ ለልጆቻችሁ ብዙ ደስታና ድል በመዋእለ-ህጻናትና በትምህርት ቤቶች እንድታገኙ መልካም ምኞት እንመኝላችኋለን።

ወይዘሮ ኢረነ ኣልት (Frau Irene Alt)
የኣገርና፣ የቤተ-ሰብ ግንኝነትና፣ የወጣቶችና፣ የሴቶች ሚንስተር

ቬራ ራይስ: (Vera Reiß)
የኣገርና፣ የትምህርት ስነ-ጥበብና የቀኣጠባና የባህል ሚንስተር